# ሠ ቅ ዳ ላ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ | ዕትም፮ | ቀን፡ ጥር ፳፫ ፪ሺ፲

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ




## መከራ ሊያበረታ እንጂ፣ ሊያዳክም አይገባውም!

ዐማራነትና ኢትዮጵያዊነት ዛሬ ከደረሱበት ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ የደረሱት የተለያዩ መከራና ችግሮችን ተቋቁመው በማለፍ ነው። ችግሮቹ የተደጋገመ የውጭ የተስፋፊዎችና የቅኝ ገዥዎች ወረራ፣ የውስጥ የሥልጣን ግብግብ የርስ በርስ ጦርነቶች፣ ሃይማኖትን መነሻ ያደረጉ ጦርነቶችና ግጭቶች እንዲሁም የተፈጥሮ የአየር ንብረት መዛባት በሕዝቡ ኑሮ ላይ ያስከተሉት ስደት፣ መፈናቀልና መራቆት፣ በዐማራና በኢትዮጵያዊነት ላይ ከፍተኛ ችግሮች የጋረጡ ነበሩ። ዛሬም እነዚህ ችግሮችና መከራዎች በተለያየ ቅርጽና ይዘት ዐማራነትንና ኢትዮጵያነትን እየተፈታተኑት ለመሆኑ አገራችን የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ በግልጽ ያሳያል።

መከራና ችግር አበረታች እንጂ፣ አዳካሚ ሊሆን ባለመቻሉ ኢትዮጵያዊነትና ዐማራ ውኃና ወተት፣ ሰምና ፈትል ሆነው እያንዳዱ መከራ የራሱን የጥንካሬ ምንጭ በማፍለቅ፣ አንድነታቸውን የበለጠ እያጠናከሩ ከ21ኛው ክፍለዘመን ላይ ደርሰዋል። የግራኝ ወረራ በኢትዮጵያዊነት እና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ የዘመተ ከፍተኛ መከራ ነበር። ያን መከራ ግን ዐማራውና የሌሎች ነገዶች ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ ቆመው ባሳዩት ጽናትና በከፈሉት መስዋዕትነት ዐማራነት፣ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ኢትዮጵያዊነት ላይለያዩ፣ ላይዳከሙ ጠንክረው እንዲወጡ ማድረጉን ሕያው ታሪካችን ያስረዳል።

ከግራኝ አሕመድ ውድቀት በኋላ በአገሪቱ ተከስቶ የነበረው የማዕከላዊ መንግሥት መዳከምና ሥልጣን በአካባቢ የጦር አበጋዞች እጅ መግባት የአገሪቱን አንድነት ከከፍተኛ አደጋ ላይ የጣለና፣ በሕዝቡ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካ ሕይወት ላይ እጅግ ከፍተኛ መከራ የደቀነ እንደነበር ይታወቃል። ይህ መካራ ግን ኢትዮጵያዊነት አንድነትን ሊያጎለብት እንጂ፣ ሊያዳክም እንዳልገጠመ በሂደት ታይቷል። በዘመነ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ የግዛት ዘመንና ከዚያም በፊት፣ በተከታታይ የተነሱ የቱርክ፣ የግብፅና የፖርቱጋል ተስፋፊዎች በቀይባሕር ዳርቻ፣ በቦጎስ እና በሐረር ያደረጉት የመሥፋፋት ዓላማና በሕዝቡ አንድነት ላይ ሊገነቡት የነበረው የልዩነትና የብጥብጥ ግንብ በሕዝቡ የአንድነትና የነፃነት ስሜት መጎልበት የተነሳ መከራውን ተቋቁሞ ኢትዮጵያዊነት እንዲጎለብት የራሱን አሻራ ትቶ አልፏል። ለዚህም በጉራ፤ በጉንደት፣ በከሰላ፣ በሣር ውኃ፤ በጎንደር፣ በመተማ፣ በዜይላ ወዘተ የጦር ሜዳዎች የተከፈለው መስዋዕትነትና ያስከተለው መከራ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን አዳብሮ ለቀጣዩ ትውልድ ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ መሆኑ አይዘነጋም።

# መከራ ሊያጠነክር እንጂ፣ ሊያዳክም አይገጥምም!

የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች መላው አፍሪካን፣ እስያንና ላቲን አሜሪካን በቅኝ ግዛታቸው ቁጥጥር ሥር ለማዋል ባካሄዱት ዙሪያገብ ከበባና በከፈቱት ጦርነት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት እንግሊዝ፣ ፈረንሳንና ጣሊያን የተለያዩ የመከራ ጫናዎችን በአገራችንና በሕዝባችን ላይ መጫናቸው ይታወቃል። መከራ ግን ሊያጠነክር እንጂ፣ ሊያዳክም ስለማይከሰት፣ ጀግኖች አባቶቻችን በአባ ዳኘው ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ ብጡል  ብልኅ መሪነት በዘመኑ እጅግ ዘመናዊ የተባለውን አውሮፓዊ ጦር አምባላጌ፣ መቀሌና ዐድዋ ላይ በተከታታይ ድል በመንሳት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጠንክረው፣ ተሸለውና ዳብረው እንዲወጡ ያደረገ መሆኑን አንጸባራቂው ታሪካችን ያስረዳል። መከራ ሊያጠናክር እንጂ፣ ሊያዳክም አይገጥምም እና ከዐድዋ ድል በኋላ ኢትዮጵያ በአፍሪካ አሕጉር ብቸኛ ነፃ ሕዝብና አገር ከመሆኗም ባሻገር፣ ለአፍሪካውያንና በቅኝ ግዛት ሥር ይማቅቁ ለነበሩ የጥቁር ዓለም ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲል፣ የትግል ወኔ፣ የማንነት መገለጫና ከመከራ ጠንክሮ የመውጣት አርያ በመሆን እንዳገለገለች የእያንዳንዱ ነፃነት ታጋይ ሕዝብ በኩራት የሚናገረው ነው። የአዲሶቹ ነፃ አፍሪካዊ አገሮች ሰንደቅ ዓላማ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ መገለጫ የሆኑት ቀለሞች አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ቀለም መሆን ምስጢሩ፣ ኢትዮጵያ በመከራ መሀል ጠንክራ የወጣች ነፃ አገር መሆኗን ማሳያ ነው።

በዐድዋ ድል ቅስሙ የተሰበረው የነጩ ዓለም፣ ከሁሉም በላይ የአውሮፓ ቅኝ ገዥ ኃይሎች፣ «ይህቺ ባቁላ ካደረች አትቆረጠምም» በሚል ሥጋት ቅኝ ገዥው ጣሊያን ዐድዋ ላይ የተኮናነበውን ሽንፈት፣ የደረሰበትን ውርደት፣ ኪሣራና ይህም በቅኝ ገዥ አውሮፓውያን ላይ ያሳደረውን የተደፈርን ቁጭት ቂም በቀል እንዲወጣ ለዳግም ወረራ እንዲዘጋጅ አበረታቱት። የመንግሥታቱ ማኅበርን ደንብ በመጣስ እንግሊዝና ፈረንሳይ ከሞሶሎኒ ጎን ቆሙ። የሮማው ካቶሊክ ፓፓም የጣሊያን ሕዝብ ከሞሶሎኒ ጎን እንዲቆም ቡራኬ ሰጠ። ለሥራ አጡ የጣሊያን ሕዝብ ከቀይ ባሕር ዳርቻ በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገች አገር አለች፤ ያችን የራስህ ለማድረግ ተሰለፍ ብለው ፓፓውና ሞሶሎኒ ቀሰቀሱ። ይህም ለኢትዮጵያና ሕዝቧ፣ ከሁሉም በላይ በዐማራው ላይ ከፍተኛ የሆነ መከራ ሰንቆ፣ የቂም በቀል ቂም ቋጥሮ የተንቀሳቀሰው የፋሽት ጦር በአየር በመርዝ ጋዝ፣ በመሬት በመድፍና በአዳፍኔ በመታገዝ ለአምስት ዓመታት ማለትም ከ1928 እስከ 1933  በጎንደር ክፍለሀገር ደግሞ ለስድስት አመታት(1928—1934) እጅግ ዘግናኝ የሆነ መከራና ፍዳ በሕዝቡ ላይ አደረሰ። አገሪቱን በስድት የቋንቋ መስፈርቶች ከፍሎ አንዱ የሌላው ጠላት እንዲሆን፣ የኦርቶዶክ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲዳከምና እንዲጠፋ፣ ዐማራ የተሰኘው ነገድ ራሱ ዐማራ ብሎ ከከለለት ክልል ውጭ በቀሩት እንዳይኖር የዘር ማጽዳት ዘመቻ ከፈተበት። በዚህ ፖሊሲው መሠረትም «ጋላ-ሲዳማ» እና ሐረር ብሎ በከለላቸው ክልሎች ይኖሩ የነበሩ ከስምንት መቶ ሺ(800,000) በላይ ዐማሮችን አፈነቃለ። በየትኛውም ክልል ዐማራው ለመንግሥት ሥራ የማይፈለግ የሁሉም ጠላት ተደርጎ እንዲቆጠር ቀሰቀሰ። ይህም በኢትዮጵያዊነት፣ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ከሁሉም በላይ በዐማራው ነገድ ላይ የተጫነ ከፍተኛ መከራና ሥቃይ ነበር። ይህ መከራና ሥቃይ ግን፣ ኢትዮጵያዊነትን፣ ኦርቶዶክስ ሃይማኖትንና ዐማራነትን የበለጠ እንዲጠናከሩ፣ እንዲጎለብቱ አደረገ እንጂ፣ እንዲዳከሙ አላደረገም። የደረሰባቸውን መከራ ተቋቁመው፣ ኃይላቸውን አጠናክረው የገጠሟቸውን መከራዎች ፊት ለፊት ተጋጥመው የበለጠ ጠንክረው በመውጣት ጠፊነታቸውን ሳይሆን ፣ዳብረው ቀጣይ መሆናቸውን ለዓለም ሕዝብ አሳይተዋል። መከራ ሊያጠነክር እንጂ፣ ሊያዳክም አይፈጠርም የምንለው ለዚህ ነው።

ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነት፣ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት እና የዐማራው ነገድ ከላይ በተከታታይ የገጠሙዋቸውን መከራዎችና ፈተናዎች በጽናት ታግለው፣ መካራዎቹ እያጠናከሯቸው እንጂ፣ እያዳከሟቸው እንዳልመጡ ለማሳየት ሞክረናል። መከራዎቹ አጠናከሯቸው ስንል ግን በዕድገታቸው ግሥጋሤ ላይ መሰናክል አልሆኑም፣ ለተሻለ ዕድገትና ሥልጣኔ ይውል የነበረ ገንዘብ፣ የሰው ኃይል እና ዕውቀት የነበረ ማንነትና አንድነትን ለማስጠበቅ አልዋለም እያልን አለመሆኑ መታወቅ አለበት። እያልን ያለነው ፣መከራው ማንነታቸውን አላስለወጠውም፣ እንዳውም የበለጠ እያጠናከራቸው መጣ ነው።

ኢትዮጵያዊነት፣ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ዐማራ የተሰኙት መከራ ተለይቷቸው የማያውቅ በመሆኑ፣ ካለፉት 40 እና 50 ዓመታት ውስጥም ተመሳሳይ መከራ እያስተገዱ ይገኛሉ። የመጀመሪያው ርዕዮተ-ዓለም ወለድ የሆነው የምሥራቁ ዓለም የዓለም አመለካከት ተካይታይ የሆነው ትውልድ፣ ነባሩን የሕዝብ አንድነትና የኢትዮጵያዊነት የወል ዕሴቶችን በሚገድ መልኩ፣ ሕዝቡን በገዥና በተገዥ፣ በጨቋንና ተጨቋኝ መደቦች ፣እንዲሁም በጨቋኝና ተጨቋኝ ብሔሮች በመከፋፈል አንዱን የሌላው ጠላት አድርጎ በመፈረጅ እርስ በርሱ እንዲጠፋፋ የተደረገበት ሂደት፣ የታዳጊውን አገር ተረካቢ ትውልድ ግራ ቀኝ አቁሞ ደም ያቃባ፣ ትውልድን ለዕልቂት የዳረገ መከራ ሕዝቡ መሸከሙ አይዘነጋም።

# መከራ ሊያበረታ እንጂ፣ ሊያዳክም አይገጥምም!

ይህ የአብዮትና የፀረ-አብዮት ዘመን በመባል የሚታወቅ የ17 ዓመት የደርግ አገዛዝ ኢትዮጵያውያን ከርዕዮተ-ዓለም ዘለው በቃላት አጠቃቀም ልዩነት ቃታ የተሳሳቡበት ዘመን በመሆኑ፣ በአገሪቱና በሕዝቡ አንድነት ላይ ከባድ መከራን ያሸከመ እንደነበር ማንም ይስተዋል አይባልም።

«ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል» የሚሉት የአባቶቻችን አባባል ዕውን ሆኖ፣ ኢትዮጵያውያን ባመኑበት መንገድ ተደራጅተው፣ ያሹትን ርዕዮት በማቀንቀን ርስ በራሳቸው ሲፋተጉ፣ የሞሶሎኒ ግርፍ የሆኑት የዐድዋ የባንዳ ልጆች ስብስብ ጣሊያን ሞክሮት ሳይሳካለት የቀረውን ኢትዮጵያን የመበታተን፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የማካዳከምና የማጥፋት፣ እንዲሁም የዐማራን ነገድ ቢቻል ማጥፋት ካልተቻለ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ዙሪያ ድርሽ እንዳይል አናሳና ተዋራጅ እንዲሆን ማድረግ የሚለውን ዕቅዱን በትግሬ-ወያኔ አማካኝነት እንዲያሳካ ሠፊ በር ከፈተ። በመሆኑም የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም የተነሳ ዓለም በአንድ ልዕለ ኃያል አገር ተጽዕኖ ውስጥ እንድተገባ መሆን፣ የሶሻሊዝምን የዕድገት ፈለግ እንከተላለን በማለት የተሰለፉትን አገሮች ያለአጋር አስቀራቸው። ይህም በመሆኑ የደርግ አገዛዝ በውስጥ በገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖች የዕርዳ ተራዳ ግብግብ፣ በሌላ በኩል የአንድነት ኃይሉ መከፋፈልና አንድ ጠንካራ ኃይል ሆኖ አለመቆም ለአገዛዙ መውደቅ ከፍተኛ የሆነ ሚና መጫወቱ ይታወቃል። ይህ አጋጣሚ ለገንጣይ አስገንጣዮቹ የሻዕቢያ፤ የትግሬ-ወያኔና የኦነግ ቡድኖች ሰርግና ምላሽ ሆነላቸው።

ይህ አጋጣሚ ለገንጣይ አስገንጣዮቹ ቡድኖች ሰርግና ምላሽ የመሆኑን ያህል፣ ለኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነት የወል ዕሴቶች፣ ለዐማራው ነገድና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ከፍተኛ የሆነ መከራን ያስከተለ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ኅልውናዊ ክስተት ሆነ። ይህ ክስተት ኢትዮጵያ እንደአገር መነሻ መሠረቷን ባሕረ-ነጋሽ ግዛቷ እንዲገነጠልና የባዕድ ግዛት እንድትሆን አደረገ። የአገሪቱ ተፈጥሮአዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ የሆነውን የቀይባሕር የሺ ኪሎሜትር የባርሕር በር ባለቤትነቷን አጣች። የወጭና የገቢ ንግዷ በሌሎች አገሮች መልካም ፈቃድ ላይ እንዲመሠረት ተደረገ። ለዘመናት ተዋልደው፣ ተስማምተውና በአንድነት የኢትዮጵያን አገራዊነት በደም አጥንታቸው አጽንተው የኖሩ ነገድና ጎሳዎችን አንዱ የሌላው ጠላት እንደሆነ በመፈረጅ ባሻቸው ጊዜ መገንጠል እንዲችሉ የሚያደርግ ከፋፋይና አገር አጥፊ ሕገ-መንግሥት ተብየ አቋቋሙ። ሁሉም ነገዶች ዐማራው ጠላታቸው እንደሆነ በመስበክ ሁሉም በዐማራው ላይ ክንዱን እንዲያነሳ ተፈቀደ። በዚህም በዐማራው ላይ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እንዲፈጠምበት ተደረገ። በዚህም የተነሳ ከ5 ሚሊዮን በላይ ዐማራ ከምድረ ገጽ እንዲጠፋ ሆነ።

የኢትዮጵያ ጥፋት የሚፋጠነው፣ የትግሬ-ወያኔ የሥልጣን ዘመን የሚራዘመው በዐማራና በኦሮሞ ነገዶች ፍቺና ጠላትነት ነው በማለት ሁለቱን የኢትዮጵያዊነት ምሰሶና መሠረት የሆኑትን፣ በቁጥር ከሌሎች ነገዶች አንፃር ብዛት ያላቸውን ነገዶች የሚለያዩ በሀሰት ላይ የተመሠረቱ ድርሳኖችን በመድረስ ለማቃቃርና እስከ ወዲያኛው ሊገናኙ እንዳይችሉ የሚያስችሉ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ሥራዎችን አሰራጩ። በሻዕቢያው ሰላይ ተስፋዬ ገብረአብ የተደረሰውን ኦሮሞ በዐማራው ላይ ቋሚ ጥላቻ ይዞ እንዲያጠፋው የሚያደርግ «አኖሌ» የተሰኘ ሀውልት» እንዲቆም ተደረገ። በነዚህ አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ የተሳቡ ቡድኖችና ግለሰቦች በዐማራ ወንድም እህታቸው ላይ የመከራ ጫናን ከማክበድ አልፎ በግፍ እንዲገደል አደረጉ።

የኢትዮጵያ ኢርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲዳከም ብዙ እርቀት የተጓዘ ሤራ ወያኔ ሠራ። የሃይማኖቱ ተከታይ ሕዝብ ከሁለትና ከሦስት እንዲከፈል አደረገ። ይህም በአማኙ ላይ ከፍተኛ የሆነ ከሥነልቦና እስከ አካላዊ ጥቃት የደረሰ መከራ ተሸካሚ እንዲሆን ተደረገ። ይህ ሁሉ መከራ በኢትዮጵያዊነት፣ በዐማራና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ተጭኖ፣ መከራው እያጠናከራቸው እንጂ፣ እያዳከማቸው አልመጣም። ትናት «እሳትና ጭድ አድርገናቸዋል» ያሏቸው ኦሮሞና ዐማራ፣ ዛሬ በአደባባይ «የኦሮሞው ደም ደማችን ነው»፣ የዐማራውና የኦሮሞው አንድነት ውኃና ወተት ነው፤ ማንም ሊለየው አይችልም በማለት ወያኔ ሊንደው የሞከረውን የሁለቱን ነገዶች አንድነት ሊናድ እንደማይችል፣ በአንፃሩ እያጠናከረው እንደመጣ ሁኔታዎች እያሳዩ ነው።

«ዐማራ መንገድ ላይ ቁጭ ብሎ ሲለምን ማየት እፈልጋለሁ» በማለት ጥላቻውን በአደባባይ በይፋ የገለጸው መለስ ዜናዊ፣ የዐማራውን ፈጽሞ መደኸየት ሳያይ እርሱ ቀድሞ አፈር ሆኗል። እንዲለምን የተመኘለት ዐማራ ለወያኔ ኅልውና የጉረሮ አጥንት ሆኖ እያስቸገረው ስናይ መከራ ሊያጠንከር እንጂ፣ ሊያዳክም እንደማይገጥም እያየን ነው።

# ሠከቡ ሊያበሩታ እንጁ፣ ሊያጸከም እፀገጥምም!

«ዐማራን እንደ ሢጋራ አጭሰን ጥለን ረግጠነዋል» ሲል የተመጻደቀው ስየ አብርሃ፣ ዐማራው የገጠመውን ክፉ መከራ በትዕግሥትና በማስተዋል ተቋቁሞ፣ ይኸውና ዛሬ የበለጠ በዐማራዊ ማንነቱ ኮርቶና ጠንክሮ የወያኔ የጭቃ እሾህ ሆኖበት፣ የሚይዝ የሚጨብጠውን አሳጥቶታል። የዐማራው መጠንከር የወያኔ የግፍ አገዛዝ ውድቀት ደወል መሆኑ ማሳያው፣ ጎንደር ላይ በደመቀ ዘውዱ የተተኮሰችው ጥይት ፋና ወጊ ሆና፣ ዐማራው በመከራው መሃል ተጠናክሮ የመውጣት ባህሉን እያረጋገጠበት ያለ ሂደት መሆኑ በይፋ እየታየነው።

«ዐማራውንና ኦርቶዶክስ አከርካሪውን ሰብረን ጥለነዋል» ሲል ሥብሃት ነጋ በትዕቢት ተወጥሮ የተናገረው፣ዛሬ ዐማራው አከርካሪው ቀርቶ ቃታ የሚስብበት የእጣቱ ጥፍር ያልተሰበረ ሆኖ፣ ለትዕቢተኞቹ ማንነቱንና ጥንካሬውን፣ በመከራው መሃል የገዛውን ብርታቱን እያሳያቸው መሆኑ፣ እያንዳንዱ መከራ፣ ሊያጠነክር እንጂ፣ ሊያዳክም የማይመጣ መሆኑን ጉልህ ማሳያ ነው።

«ገድለን የቀበርነውን ዐማራ አታንሱብን» ሲል ሣሞራ የኑስ በዐማራው ላይ የቱን ያህል ጥላቻ እንዳለው፣ በጥላቻውም ያለርኅራኄ ዐማራውን ሁሉ ገድሎ መጨረሱን እርግጠኛ ሆኖ፣ የዐማራ ስም ሲነሳ ከየት መጥቶ፣ ገድለን ጨርሰነው የል በማለት በኩራት የተናገረው፣ዛሬ ዐማራው እንደክርስቶስ መቃብሩን ገልብጦ፣ ከሙታን ተራ ተለይቶ በመውጣት፣ የወያኔ መቅሰፍት መሆኑን በተግባር እያሳየ ነው። ይህም ከመከራ መካከል የሚገኝ ጥንካሬ ነው።

«ከዚህ በፊት የነበሩ ጦርነቶች በትግራይ መሬቶች ላይ ነበሩ፤ አሁን ግን ጦርነቱን ለዐማሮች ቤታቸው ድረስ ወስደንላቸዋል» በማለት የተመጻደቀው ዐባይ ወልዱ፣ ዛሬ ዐማራውና ኦሮሞው የሚያደርገው ትግል ለመብቱና ለነፃነቱ፣ እንዲሁም ለኅልውናው ሲል በየደጁ መሆኑ ዕውነት ነው። ይህም የዐማራውንና የኢትዮጵያዊነትን ከመከራ  ጠንክሮ የመውጣት ባህል መገለጫ ከመሆን አልፎ፣ ይህ ለራስ ኅልውና መጠበቅ በእያንዳንዱ የዐማራና የኦሮሞ ደጅ የሚደረግ ጦርነት፣ የትግራይ ሕዝብ አሰላለፉን ካላሳመረ ነገ በነርሱ በር ላይ ጦርነቱ ሊከፈት የማይችልበት ሁኔታ ፈጽሞ አለመኖሩን የሚያረጋግጥ ነገር የለም። በመከራ ውስጥ ጠንክሮ መውጣት ግቡም የተነጠቁ ማንነቶችን፣ ሀብትና ንብት ማስመለስ ነውና፣ ዐባይ በፎለለበት አደባባይ ዛሬ ገና ዐማራው ሰይፉን ከአፎቱ ሳይመዝ ደብቁኝ፣ ደብቁኝ እያለ እንዳለ እያስተዋል ነው።

«ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነፍጠኛ ዐማራን እናጠፋለን» በማለት ቴዎድሮስ አድኃኖም የፎከረበት፣ ዐማራው ፈጽሞ ሳይጠፋ፣ አጥፊውን ለማጥፋት ተጠናክሮ መመከቱን መያያዙን ስናጤን፣ ጥንካሬ ከመከራ የሚመነጭ እንደሆነ እንረዳለን። ከሁሉም በላይ«ትግሬ ማለት ሊገፋ የማይችል ተራራ ነው»በማለት የሚመጻደቁት ወያኔዎች፣ ይህ ከመከራ ውስጥ የሚወለድ ጥናካሬ የወያኔን የበላይነት አሽቀንጥሮ በመጣል የኢትዮጵያዊነት አንድነትን አጠናክሮ እንደሚደመደም መጠራጠር አይቻልም። ለዚህ ዕውን መሆንም የኦሮሞና የዐማራ ፖለቲከኞች ወደ ዕውነተኛ ኅሊናቸው በመመለስ ጠብ የሌላቸውን ነገዶች ከማጣላት ተቆጥበው በነባር አንድነታቸው ላይ በመመሥረት የአንድነታቸው ቅንቅን የሆነውን ወያኔ ለማስወገድ ከመቸውም በበለጠ አንድነታቸውን በማጎልበት፣ የተጫነባቸው መከራ፣ የብርታታቸው ምንጭ እንጂ፣ ሊያዳከማቸው እንዳልገጠማቸው ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም ሕዝቡ የጀመረውን የአንድነት ትግል ግለቱ እንዳይበርድ፣ ሙቀቱ እንዳይቀዘዝቅዝ በማደረግ፣ ለ26 ዓመታት የተጫነባቸው መከራ፣ ተጠናክረው የመውጫቸው መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ቆጥረው፣ የመከራቸው ሁሉ ምንጭ የሆነውን የትግሬ ወያኔ አገዛዝ፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ መንጭቆ ለመጣል የተፋፋመው ትግል ለግብ እንዲበቃ ለማድረግ፣ የሁለቱ ታላላቅ ነገዶች የፖለቲካ፣ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት አመራሮች ከምንጊዜው በበለጠ ተቀራርበው ሊሠሩ ይገባል።

## የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!